# ወያኔ ቱርኪ ነው !!!



ማዕበል ነው ሕዝቡ፣ የሚነድ እሳት፣

የማይንበረከክ፣ ላገሩ የሚሞት፣

ሆ ብሎ ተነስቷል፣ ከዳር እስከዳር፣

ቆራጥ ነው ሕዝባችን፣ ባንድ ላይ የሚያብር፣

መስሎሽ ነበር አንቺ ፣ እሳቱ የጠፋ፣

ያገኘሽ እረፍት፣ የሚሰጥሽ ተስፋ፣

ወደ ኋላ አይልም ፣ አንቺን ሳያጠፋ፣

በነቂስ ሲወጣ ፣ ሆ ብሎ ሲነሳ፣

እንደ አሸን ሲፈላ ፣ እንደዚያ እያገሳ፣

ሱናሜ መሆኑን ፣ ወያኔ እንዳትረሳ፣

ሆ ብሎ የተነሳ ፣ በድል እስኪመለስ፣

ቃል ኪዳን ገብተናል፣ ቤታችን ላንገባ፣

የፈሰሰውን ደም ያነባውን ፣ እንባ፣

ሕዝቡን ሳናብሰው ፣ አንዘልቅም ከአምባ።

መይሳው ከምድረ ስዊድን

2015-12-20